# የ TB የደም ምርምራ ምንድን ነው?

የኢንተርፌሮን ጋማ ልቀት ኤሴይ ወይም IGRA በመባል የሚታወቀው የሳንባ ነቀርሳ (TB) የደም ምርመራ በሰውነትዎ ውስጥየ TB ተዋህሲያን እንዳሉ የሚያውቁበት አንዱ መንገድ ነው። ሁለት አሁን ላይ ያሉ የደም ምርመራዎች QuantiFERON®-TB እና T-SPOT®.TB ናቸው።

## የሚከተሉትን ካሟሉ የ TB ምርመራ ማድረግ አለብዎት፦

- ንቁ ተላላፊ TB ካለበት ሰው ጋር ተደጋጋሚ የቅርብ ንክኪ ከነበርዎት፣
- በርካታ ሰዎች በ TB የተያዙበት ሐገር ውስጥ ከኖሩ፣
- የነርስንግ እንክብካቤ ቤት፣ ክሊኒክ፣ ሆስፒታል፣ እስር ቤት፣ ወይም የቤት አልባ መጠለያ ውስጥ የሚሰሩ ወይም የሚኖሩ ከሆነ፣
- ወይም በሽታ የመከላከል አቅምዎ በጣም ጠንካራ ካልሆነ።

ከ2 ዓመት በታች ያሉ ልጆች ከ TB የደም ምርመራ የ TB የቆዳ ምርመራ ማድረግ አለባቸው።

## የ TB የደም ምርመራ እንዴት ማድረግ እችላለሁ?

የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ። ትንሽ የደም መጠን በመውሰድ ወደ ቤተ ሙከራ ይልኩታል። በጥቂት ቀናት ውስጥ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ የምርመራ ውጤትዎ ኔጌቲቭ ወይም ፖዘቲቭ መሆኑን መናገር አለበት።

## የTB ምርመራ ውጤቴ ኔጌቲቭ ቢሆንስ?

ኔጌቲቭ የ TB የደም ምርመራ ውጤት ብዙ ጊዜ በሰውነትዎ ውስጥ የTB ተህዋሲያን የሉም ማለት ነው።

## የTB ምርመራ ውጤቴ ፖዘቲቭ ቢሆንስ?

ፖዘቲቭ የ TB የደም ምርመራ ውጤት በሰውነትዎ ውስጥ የ TB ተህዋሲያን አሉ ማለት ሊሆን ይችላል። ፖዘቲቭ የ TB ደም ምርመራ ያለባቸው አብዛኛዎቹ ሰዎች ድብቅ የ TB በሽታ አለባቸው። እርግጠኛ ለመሆን፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይመረምርዎታል እንዲሁ የደረት ራጅ ያነሳዎታል። ድብቅ የTB በሽታ ወይም ንቁ TB እንዳለብዎት ለማወቅ ሌሎች ምርመራዎች ሊያስፈልግዎት ይችላል።

## ድብቅ የ TB በሽታ ምንድን ነው?

ሁለት የTB ደረጃዎች አሉ። ሁለቱም ደረጃዎች በመድሐኒት መታከም ይችላሉ።

የTB ተህዋሲያን ወደ ሰውነትዎ ሲገቡ፣ ድብቅ የTB በሽታ ያስከትላሉ። ሕክምና ካላገኙ፣ ድብቅ የTB በሽታ ንቁ TB ሊሆን ይችላል።

| **ደረጃ 1 –**<br>**ድብቅ የTB በሽታ** | **ደረጃ 2 –**<br>**ንቁ TB** |
|---|---|
| የTB ተህዋሲያን በሰውነትዎ ውስጥ የተኙ ('እንቅልፍ ውስጥ ያሉ') ናቸው። ይህ ደረጃ ለረዥም ጊዜ – ምናልባትም በርካታ ዓመታት ሊቆይ ይችላል | የ TB ተህዋሲያን ንቁ ('የነቁ') እና እየተሰራጩ ያሉ ናቸው። በሰውነትዎ ውስጥ ያለን ህብረ ህዋስ እየጎዱ ያሉ ናቸው። |
| የታመሙ አይመስሉም ወይም የህመም ስሜት አይሰማዎትም። የደረት ራጅ ውጤትዎ ብዙ ጊዜ መደበኛ ነው። | ብዙ ጊዜ የህመም ስሜት ይሰማዎታል። የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ የ TB ተህዋሲያን ሰውነትዎን የት እየጎዱት እንዳለ ለማግኘት ልዩ ምርመራዎች ያደርጋል። |
| የ TB ተህዋሲያንን ወደ ሰዎች ማስተላለፍ አይችሉም። | የ TB ተህዋሲያን ሳንባዎ ውስጥ ከሆኑ፣ በሳል፣ በማስነጠስ፣ በማውራት፣ ወይም በመዘፈን ወደ ሌሎች ሰዎች TB ሊያሰራጩ ይችላሉ። |
| አንድ ወይም ሁለት መድሃኒቶችን ከሶስት እስከ አራት ወራት በመውሰድ ይታከማል። | ቢያንስ ለስድስት ወራት ከሶስት እስከ አራት መድሐኒቶች በመውሰድ ይታከማል። |

## የ BCG ክትባት ወስጄ ቢሆንስ?

የBCG ክትባት (የ TB ክትባት) ሕጻናት ልችጆ በንቁ TB በጣም ከመታመም ለመከላከል ይረዳል። ሰዎች ዕድሜያቸው በጨመረ ቁጥር ይህ ጥበቃ ይቀንሳል።

የ BCG ክትትባ የወሰዱ ሰዎች በድብቅ የTB በሽታ እንዲሁም በንቁ TB ሊያዙ ይችላሉ።

የ BCG ክትባት ወስደው ከነበረ እንዲሁም የTB የደም ምርመራ ወይም የTB የቆዳ ምርመራ ለማድረግ ምርጫዎ ከሆነ፣ የ TB የደም ምርመራ ማድረግ ለእርስዎ የተሻለ ነው። ምክንያቱም የTB የደም ምርመ በ BCG ክትባት ተጽዕኖ አይደረግበትም። ይህም ማለት የTB የደም ምርመራዎ ፖዘቲቭ የሚሆነው ሰውነትዎ ውስጥ የ TB ተህዋሲያን ካሉ ብቻ ነው።

የእርስዎን ጤና እንዲሁም የቤተሰብዎን ጤና ይጠብቁ – የTB የደም ምርመራ ያድርጉ!

Minnesota Department of Health
Tuberculosis (TB) Prevention and Control
1-877-676-5414 or 651-201-5414
www.health.state.mn.us/tb

02/24

*ይህን መረጃ በተለየየ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደሚከተለው ይደውሉ፡- 651-201-5414።*